# ትውፊት

## ኢትዮጵያዊት ሆሜር /1889-1978ዓ.ም/
## (እማሆይ ገላነሽ - ማየት የተሳናቸው የቅኔ መምህርት

ያሲን ዑመር
ብ/ቤተ መጻሕፍትና ቤ/ መዛግብት ኤጀንሲ የጥናትና ማስተዋወቅ ከፍተኛ ኤክስፐርት

### መግቢያ

የሀገራችን የቅኔ ሊቃውንት ታሪክና ገድል ሲነገር በረቀቀና በመጠቀ የቅኔ ችሎታቸው ስመጥር የነበሩት ኢትዮጵያውያት ስምም አብሮ ይነሳል፡፡ በተለይ ደግሞ ማየት የተሳናቸው የቅኔ ሊቅ በመሆናቸው ኢትዮጵያዊቷ ሆሜር ሊባሉ የሚችሉት እማሆይ ገላነሽ ሐዲስ እና ወተዜር ፈንታ የተባሉት የሴት ባለቅኔ ስሞች ጎልተው ይጠቀሳሉ፡፡

የቀደሙት እናቶቻችን የነበራቸውን ተሰጥዖ ተጠቅመው ዛሬ በየአካባቢው በየቋንቋው ለዘፈን ሆነ ለልቅሶ ኅብረተሰቡ የሚጠቀምበትን ሥነቃል ትተውልን አልፈዋል፡፡ በኀሊናቸው ወደህዋ ዘልቀውና መጥቀው፣ አዕምሮአቸውን አስጨንቀው ጭንቅላታቸውን አልበውና ጨምቀው ቅኔን ያህል የፈጠራ ጥበብ በምልዐተ አእምሮአቸው ደርሰውልናል፡፡ የቅኔን ምሥጢር አዝመራ በጥበብ ጎተራ ሞልተው አትረፍርፈውልናል፡፡ ትርጓሜን በእንድምታ ቅኔን በሐተታ እያመሠጠሩና እያመራመሩ በጥበብ ሰማይ ላይ ደምቀው ብርሃነ ዕውቀት ከዋክብ ቸውን አብርተውልናል፡፡

ኀሊናን የሚኮረኩር ሰምና ወርቅ/ ኅብረቃል/ አበው "ቋንጣ የለውም" የሚሉትን የቅኔ ጥበብ ትተውልን ካለፉት ኢትዮጵያውያን/ያት መካከል በዚህች አጭር መጣጥፍ የእማሆይ ገለነሽ የሴት ባለቅኔነት ታሪክና ገድል ለመዘከር ጥረት ይደረጋል፡፡ በጥረቱም እማሆይ ገላነሽ ማን ናቸው? ሕጻኗ ገላነሽ የት ተማረች ? ለአቅመ ሔዋን የበቃችው ገላነሽ ግላዊ ርዕዮተ ዓለም (Personal ideology) እና ተፈጥሮ እንዴት ይገለፃል? እማሆይ ገላነሽ የቅኔ አዝመራን ለፍሬ ለማብቃት ስንት ደቀ መዛሙርት አስተማሩ? የእማሆይ ልዩ ችሎታ ምንድነው? የሚሉት ጥያቄዎች ይነሳሉ ፤ በቅደም ተከተላቸውም ምላሽ ያገኛሉ፡፡

### እማሆይ ገላነሽ ማን ናቸው?

እማሆይ ገላነሽ በ1889 ዓ.ም በምዕራብ ጉጃም ሀገረ ስብከት ይልማና ዴንሣ ወረዳ ፅላሎ አማኑኤል ደብር ተወለዱ፡፡ እማሆይ ገላነሽን የሴት ባለቅኔነት ታሪክና ገድል ለመዘከር መለስ ብሎ የ ምቦቀቅላዋ ገላነሽን አስደናቂ ተፈጥሮ መቃኘት አስፈላጊና ተገቢም ነው፡፡ ሕጻንዋ ገላነሽ በጨቅላ ዕድሜዋ ሳታስታጉል እናቷን ተከትላ በአጥቢያቸው የሚገኘውን የቅዱስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን መሳለም ታዘወትር ነበር፡፡ በተለይ ዘወትር እሁድ እሁድ የዕለቱ የሃይማኖት ትምህርት ካበቃ በሁዋላ የሚከናወነውን የቅኔ ዘረፋ በተመስጦ ትከታተል ነበር፡፡ ሕጻኗ ገላነሽ በቅኔ ዘረፋው በመመስጥ አልተወሰነችም ፡፡ ከዕለ ት ባንደኛ ዋ፣የደብረ ታቦር ዕለት እናቷን ተከትላ ከመጀመሪያው ረድፍ በተቀመጠችበት አስደናቂ ነገር ተከሠተ፡፡ የዕለቱ የቅኔ ዘረፋ ተረኛ የነበሩት የገላነሽ አባት ቄሰ ገበዝ ሐዲስ ፣ ቅኔ ዘረፋውን ጀምረው "በታቦርሂ አመነቀፀ መለኮትከ ፈረስ" እያሉ ሲቀኙ የ8 ዓመትዋ ሕጻን ገላነሽ ከተቀመጠችበት እመር ብላ ተነሳች ፡፡ አባቷ የጀመሩትን ቅኔ ካፋቸው ነጥቃ "ኢክህሉ ሰሂቢቶ ሙሴ ወኤልያስ" ብላ ጨረሰችውና ህዝበ አዳምን አስደመመችው፡፡

**ትርጉም፣**

"መለኮት ፈረስህ በደብረ ታቦር በዘለለ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ሊስቡት አልቻሉም" ማለት ነው፡፡

**ሰሙ** ፣ፈረስ በዘለለ ጊዜ ለመሳብ ያስቸግራል

**ወርቁ**፣ጌታ በደብረ ታቦር ብረሃነ መለኮቱን በገለጠ ጊዜ ነቢያት ቀና ብለው ማየት አልቻሉም ፡፡ ሙሴ ወደ መሬት አንገቱን ደፋ፡፡ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡

"ሴት በማጀት ወንድ በችሎት" የሚለው ሥር የሰደደ ነባር ብሂል በተንሰራፋበት በተለይ በዚያ ዘመን በሕጻንዋ ገላነሽ ያልተለመደ ድርጊት ምዕመናን ተደናገጡ፤ በቅኔዋ ረቂቅነት ተመሰጡ፤ ለሕጻንዋ የቅኔ ችሎታ የ«ይደልዋ» አድናቆታቸውን ገለጡ፡፡

ወደ ገጽ 25 ዞሯል

# ኢትዮጵያዊት ሆሜር ...

ከ ገፅ 20 የቀጠለ

በአስገራሚ የቅኔ ችሎታዋ የምዕመናን ሙገሳና አድናቆት የጎረፈላትና "ትደግ ትመንደግ፣ ከዓይን ያውጣት" የሚል ምርቃት የተዥጎደጎደላት ሕጻንዋ ገላነሽ በዚያው ዓመት አንድ አስደንጋጭ በሽታ ገጠማት ። በድንገተኛ ሕመም ተለከፈች። በደዌ ዳኛ ተይዛ የአልጋ ቁራኛ ሆነች። በፈጣሪዋ ተአምር ከሞት ብትተርፍም ገና የ8 ዓመት ሕጻን እያለች የዓይኖቿን ብርሃን አጣች።በገላነሽ የዓይኖቿን ብርሃን ማጣት መላ ቤተሰብዋና የሚያውቃት የመንደሩ ሁሉ ሰው ተደናገጠ፣ ክፋኛም ከልብ አዘነ። አባቷ ቄሰ ገበዝ ሐዲስ ግን የቅኔ ተሰጥዖ ባላት ልጃቸው ተስፋ አልቆረጡም። ሕጻንዋ ገላነሽ በልጅነቷ ያጣችውን የዓይን ብረርን በቅኔ ጥበብ ብርሃን ለመተካት ቆርጠው ተነሱ።

## የሕጻንዋ ገላነሽ የተማሪነት ገጽታ

ሕጻንዋ ገላነሽ ወላጅ አባቷ ቄሰ ገበዝ ሐዲስ የቅኔ ጉባኤ ተክለው በመምህርነት በሚያገለግሉበት በምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ይልማና ዴንሳ ወረዳ ውስጥ በሚገኘው ፅላሎ አማኑኤል ደብር ውስጥ የፊደል ገበታንና አቡጊዳን መቁጠር ጀመረች። ደረጃ በደረጃም መልእክተ ዩሐንስን፣ ዳዊትን፣ ውዳሴ ማርያምን ፣ ቅዳሴ ማርያምን፣ ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን ከትርጓሜያቸው፣ ቅኔንም ከነአገባቡ ተማረች። በዘመኑ የነበረው ባህላዊና ሃይማኖታዊ የትምህርት ሥርዓት የሚጠይቀውን የመመዘኛ መሥፈርት በድንቅ ብቃት አሟልታ ተመረቀች፤ ለቅኔ መምህርነት ብቁ መሆኗም ተመስክሮ ተረጋገጠላት።

## ግላዊ ርዕዮተ ዓለም (Personal ideology) እና ተያያዥ ተፈጥሮ

በአባታቸውና በሌሎች መምህሮቻቸው የዕውቀትና የቅኔ ጥበብ ብርሃን እየተመሩ፣ የቅኔን ጥበብና ምሥጢር እየመረመሩ ያደጉት እማሆይ ገላነሽ ሴት ልጅ በማጀት ተወስና በማይምነት ጨለማ ተውጣ ማደን አግባብ አለመሆኑን መናገር ጀመሩ። "መማርም ሆነ ማስተማር ብርታትን እንጂ ፆታን አይመለከትም፤ መምህራችን ክርስቶስ ሴቶች ደቀመዛሙርቱን 'ሂዱና ትንሣዔዬን ንገሩ' ብሏቸዋል፤ ልዩነት የለም" ይሉ እንደነበር በቅርብ የሚያውቋቸው የእህታቸው ልጅ ተሾመ አዲስ ምሥክርነታቸውን እንደሰጡ ቀሲስ ከፍያለው መራሒ "ሴቶች በኢትዮጵያ" (1978) በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ ገልጸውታል።

እማሆይ በመማር ባገኙት የዕውቀት አቅምና በመንፈስ ፅናታቸው በመታገዝ ሴት ልጅ ከማጀትና ከጓዳ እንዳትወጣ ቀይዶ የያዛትን የፅልመት ግድግዳ ፣ የዘልማድ አጥርና የጎጂ ልማድ ኬላ አሽቀንጥረው ጣሉ። በዚህም በዘመናቸው ከነበሩት ሴቶች ለየት ያለ ግላዊ ርዕዮተ ዓለም እንዳላቸው አስመሠከሩ። ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሰልፈው

መሥራታቸው የኖረ እንጂ እንግዳ ነገር አለመሆኑን በአንደበታቸው መገለጽ ብቻ ሳይሆን ቃላቸውን በተግባር አውለው በአደባባይ አስመሠከሩ።

ይህ እውነታ እማሆይ ገላነሽን ከ1900ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ ስለሴቶች ዕኩልነት የተናጠል ድምፃቸውን ማሰማት የጀመሩ የለውጥ ፋና ወጊ ሊባሉ እንደሚችሉ ጉልህ ማሳያ ነው።

በሌላ በኩል ለአቅመ ሔዋን የበቃችው ገላነሽ በወግ ተሞሽራለች፤ ወልዳ ለመሳምም በቅታለች። በዚህም የትዳር ሕይወትንና የእናትነት ተፈጥሮአዊ ፀጋና በረከትን ተቋዳሽ ሆናለች።

በተመሳሳይ መልኩ እማሆይ በተፈጥሮአቸው የጸሎት ትጋት የሚታይባቸው መንፈሳዊ እናት ነበሩ። በዓለማዊው ሕይወታቸው የማስተማር ፍቅር ያላቸው የፊታቸው ፀዳል በዕውቀትና በደስታ ፈክቶ የሚታይ እንደነበሩ በቅርብ የሚያውቋቸው ይመሠክራሉ። በጣም ምሥጢር ዐዋቂ ፣ ብልህ፣ ሞክሮ ማሳካት ፣ ታግሎ ማሸነፍ የሚወዱ ሽንፈትን በጣም የሚጠሉ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል።

በዚህ መነሻነትም እማሆይ ከዓይናማዎች እኩል እየፈተሉ፣ በርካታ በቀለማት ያጌጡ ሙዳዮችንና መሶበ ወርቆችን እየሠሩ ለገበያ ያቀርቡ እንደነበርና በግል ጥረታቸው በሚያገኙት ገቢ ከባላቸው የኢኮኖሚ ጥገኝነት ነፃ መሆን እንደቻሉ በዝርዝር ተጠቅሷል። "ምን ሴት ብታውቅ፣ በወንድ ያልቅ" የሚለውን ለዘመናት ሥር ሰድዶ የቆየ ሀገርኛ ብሂል ከመሠረቱ መነቅነቅ የቻሉና በፅናትና በጥረት ከወንድ ኢኮኖሚ ጥገኝነት ሙሉ በሙሉ ነፃ መውጣት የሚቻል መሆኑን በተግባር ያስመሠከሩ ለፅናት አብነት ናቸው።

## የእማሆይ ገላነሽ የቅኔ መምህርነት ታሪክና ገድል

እማሆይ ለበርካታ ዓመታት ብሉይና ሐዲስን ባንድምታ በመተርጎምና

ወደ ገጽ 58 ዞሯል

http://www.writing.utoronto.ca/advice/specific-types-of-writing/literature-review. Health Sciences Writing Centre

Vaverka, K. and Fenn, S. http://kancrn.kckps.k12.ks.us/guide/literature.html

continued from page 53

Weissberg, R. Buker, S. 1990. Writing up Research Experimental Research Report Writing for Students of English. USA: Prentice-Hall, Inc.

Wondwossen, T. 1999. "Research Methodology for ELT Students". KCTE: Unpublished.

# Faculty Profile . . .

education sector in different ways. The issue of competence, research out put, etc are questions we would continue to ask once we feel that we have the required level of qualification for our staff. Confronting such challenges may be what this generation is destined for. In view of what we wish to see in the future, what choice do we have other than gladly accepting today's hurdles? It should not also be forgotten that, no matter what the challenges are, what distinguishes the human race from others is how much it can positively or adversely

affect the future of its species.

**References**

Altbach, P.G. and P.M. Peterson (Eds). 2007. Higher Education in the New Century: Global Challenges and Innovative Ideas. Rotterdam: Sense Publishers.

Damtew Tefera. 2003. "Scientific Communication and Research in African University:Challenges and Opportunities in the Twenty-First Century". In Damtew Tefera and P.G. Altbach (Eds) African Higher Education: An International Reference Handbook. Indianapolis: Indiana University Press.

Damtew Tefera. 2005. "Ethiopian Higher Education: Nurturing Quality Striving for Excellence" Key note Address given at the Third National Conference on Private Higher Education in Ethiopia. Addis Ababa: St. Mary's University College.

Ministry of Education (MoE). 2008. Education Statistics: Annual Abstract, 1999 E.C. 2006/2007 GC). Addis Ababa: MoE.

Teshome Yizengaw. 2007. The Ethiopian Higher Education: Creating Space for Reform. Addis Ababa:

"Partisanship is our great curse. We too readily assume that everything has two sides and that it is our duty to be on one or the other."

**James Harvey Robinson**

# ኢትዮጵያዊት ሆሜር ...

ከገጽ 25 የቀጠለ

የሊቃውንት መጻሕፍትን ተምረው በማጣጣም የቀሰሙትን ዕውቀት እንደጋን ውስጥ መብራት መና አላስቀሩትም፡፡ በተፃራሪው፣ ተወልደው ባደጉበትና በወግ በማዕረግ በተዳሩበት፣ ወልደው በሳሙበትና የሴት ባለቅኔነት አክሊል በተጎናፀፉበት ጎንጅና ጽላሎ የቅኔ ጉባኤ ተክለው በተከታታይ ለሃምሳ ሦስት ዓመታት በቅኔ መምህርነት አገልግለዋል፡፡ በዚህም ከአምስት አሠርት ዓመታት በላይ የጎንጅና የፅላሎን የቅኔ ጎዳና መርምረው፣አመሥጥረው፣ተርጉመውና አቃንተው ለ1750 ደቀመዛሙርታቸው/ የቅኔ ተማሪዎቻቸው/ የጥበብን ቀንዲል አብርተዋል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ እማሆይ 36 መሪ ጌታዎችን በቅኔ ትምህርት አሠልጥነው ለቅኔ መምህርነት ብቁ መሆናቸውን በመመሥከር ለድብትርና ወግ ማዕረግ አብቅተዋል፡፡ ከቅኔ ጥበብ ዓለም ከአስተዋወቋቸው መምህሮቻቸው የተቀበሉትን የዕውቀት ፋና ለተተኪዎቻቸው አቀብለዋል፡፡ የተቀበሉትን የመምህርትነት አደራ በአግባቡ ተወጥተዋል፡፡ ስማቸውን ከመቃብር በላይ የሚያውል ታሪክና ገድል ፈፅመዋል፡፡ የእማሆይ ገላነሽን ሊቅነት የተገነዘበው ሕዝብ ፣

"ጐንጅና ጽላሎ አንድ ነው መሬቱ፤
ጽላሎ ይበልጣል አንች ያለሽበቱ"

እያለ አድናቆቱን ሲገልፅ ኖሯል፡፡

'ለመታሰቢያቸው ባህር ዳር ከተማ ውስጥ ሙዚየም ተሠርቶላቸዋል፡፡ ምሥላቸው በትልቁ ተሰቅሏል፡፡ በጽሑፍ ሠፍረው በታሪክ ተመዝግበው የተገኙ ቅኔዎቻቸው ተሰባስበው ተቀምጠዋል' ይላሉ ሰለሞን ሐዲስ የተባሉ የአዲስ አበባ ዩኒቨስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ተማሪ በ1992 ዓ.ም. የእማሆይ ገላነሽን ግለ-ታሪክ በዳሰሱበትና ለዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፋቸው፡፡

## የእማሆይ ልዩ ችሎታ

በእማሆይ ገላነሽ የሴት ባለቅኔነት ታሪክና ገድል ውስጥ ጎልቶ የሚጠቀሰው ቅዱስ ያሬድ ከደነገጋቸው ሃያ ሁለት የቅኔ መልኮች በሰባቱ የመጠቀም ልዩችሎታቸው ነበር ፡፡ ለሀገራችን የሙዚቃ ቅኝቶች ሳይቀር አባት በሆነው ስመጥሩው ቅዱስ ያሬድ

ወደ ገጽ 64 ዞሯል

# የሕጻናት ቋንቋ ...

ከገጽ 22 የቀጠለ

ቀስ በቀስ እየተገነዘበ ይመጣል። እራሱ የሚናገራቸውንና ሌሎች የሚናገሯቸውን ድምጾች መለየት ይጀምራል።

3. The telegraphic stage :- ይህ የዕድሜ ደረጃ ከ18 እስከ 36 ወራት ያሉትን ጊዜያት ያጠቃልላል። በዚህ ጊዜ የተሟላ ትርጉም ያላቸውንና አድማጭ ሊገነዘባቸው የሚችላቸውን ዐረፍተ ነገሮች ማፍለቅ ይጀምራል። ቢሆንም ግን አያያገሮች፤ ጊዜ አመልካቾችንና ተውላጠ ስሞችን ሊዘነጉ ይችላሉ። ይህ የቋንቋ መልመድ ደረጃ ሁለት ገፅታዎች አሉት። አንደኛው ሁለት ቃላትን ማገናኘት ሲሆን ሁለተኛው ከሁለት በላይ የሆኑ ቃላትን የማያያዝ ገፅታ ነው። በማገናኘት ጊዜ ቃልን ከተወካዩ ነገር ጋር ብቻ አይደለም የሚያገናኙት - ቃላትንም ርስ በርሳቸው ማገናኘት ይጀምራሉ። በቃላት መጫወት፣ ሆሄያትን መደጋገም ፣ቃላትን ማገናኘት ተዘው ሪ ልምምዶች ይሆናሉ።ከዚህም ልምምድ ሥፍር ቁጥር የሌለው የቃላት ማገናኛ መንገድ መኖሩን ይገነዘባሉ።

4. የማያያዝ ደረጃ /connective stage/ ፤ከሦስት ያላነሱ ቃላትን ጐን ለጐን በመደርደር ጐናዊ ተዛምዶ/syntagmatic relation/ ለመፍጠር የሚጣጣሩት ነው። ከዚህም ሌላ ተውላጠ ስሞችን፣ መስተዋድዶችንና ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን የሰውነት እንቅስቃሴዎችንም የሚያሳዩት በዚህ ደረጃ ነው። በማያያዝ ሂደት ሕጻናት በመጠኑም ቢሆን ከአገልግሎትና ከመዋቅር አኩዋያ ወሰብሰብ ያሉ ዐ ረፍተ ነገሮችን ይጠቀማሉ፤ ሐተ ዊ ፣ መጠይቃዊ ፣ትዕዛዛዊ ፣ ኣጋኖኣዊ፤ ንዲሁም ነጠላ ብቻ ሳይሆን ድርብና ድብልቅ የመሳሰሉትን ማለት ነው።

5. The recursive stage: - ከ3-5 ዓመት ያለውን ጊዜ ይይዛል፤ ደረጃው ካለፉት ጋር ሲነፃፀር ላቅ ያለ የቋንቋ ችሎታ የሚታይበት ነው። አንድን ዐረፍተ ነገር በሌላ መልክ ማዋቀር የሚችሉበት የዕድሜ ክልል ነው። በተጨማሪም ከአካባቢ ፣ ከዘመድ፣ ወዘተ. የሚሰሙዋቸውን መዋቅሮችም ለይተው መናገር ይጀምራሉ።

ለማጠቃለል ያህል ከፍ ሲል በቀረበው የሕጻናት የቋንቋ ለመዳ ሂደት ለማየት ንደሞከርነው አንድ ሕጻን የትም ይወለድ፣የትም ተወልዶ የትም ይደግ፣የትም አድጎ ምንም ዓይነት ቀለምና ዘር ይኑረው ዋናው ጉዳይ ሰው መሆኑና በሰው መሃል መንቀሳቀሱ ቢያንስ የአንድ ቋንቋ ባለቤት ሊያደርገው ንደሚችል ተ ገንዝበናል። የሕጻናትን የቋንቋ አለማመድ ሥልትና አኮሁዋን መገንዘቡ ሕጻናት በየትኛው ዕድሜያቸው ንዴት ያለ የቋንቋ ክሂል ሊኖራቸው ንደሚችል መረዳት ከማስቻሉም በላይ የኛ የአዋቂዎች/ የትልልቆች/ ሚና ምን ሊሆን ወይም ላይሆን ንደሚችል አንዳች ግንዛቤ ያስጨበጣል። የኛ የትልልቆች ሚና ይህን ተፈጥሮኣዊ ሂደት በማገዝ ንጂ በማስቀረት ወይም በማደናቀፍ ረገድ ጤናማ ሥልጣን ሊኖረን ንደማይችል ከተገነዘብን ዘንድ ሕጻናት ልጆቻችን ለሚደርሱበት ወይም ንደሚደርሱበት ለሚ መነው ከፍተኛ የቋንቋ ዕደገት ደረጃ ንዲበቁ ለማስቻል ከ ኛ የሚጠበቀው በተለይ የመልካም ሥነ ምግባር ባለቤቶች ንዲሆኑ ከጎናቸው ባለመለየት ማበረ ትና በቻልነው ሁሉ ድጋፋችንን መስጠት ነው። ልጆችን ቋንቋ የማስለመድ ጣጣ የወላጆች ብቻ ቢሆን ኖሮ በገንዘብ አቅም ማጠር ምክንያት ብዙዎች የዓለም ዜጎች ዱዳ ሆነው ሊቀሩ ንደሚችሉ ስናስበው በርግጥም የተ ፈጥሮን ያልተገደበ ቸርነት በ ጅጉ ናደንቃለን። ይህ ለሌሎች ንስሳት ያልተሰጠ፣ ለኛ ለሰዎች ብቻ የተለገሠ ዕድል በአግባቡ አገልግሎት ላይ ንዲውል ዲያ የሕጻናት ልጆቻችንን የቋንቋ ለመዳ ተፈጥሮኣዊ ሂደት በማያደናቅፍ መልኩ በጥሩ ሁኔ የማሳደግ ላፊነትና ግዴ ንዳለብን በማጠቃለያው ማጠቃለያ ላይ ማስ ወሱ አግባብነት አለው።


## ዋቢ መጻሕፍት

B. Hutlovk, Elizabeth (2004). Child Development. 11th edition Tata McGraw –Hill, PLC.

___________. (2004) Development Psychology. 5tth edition Tata McGraw –Hill, PLC.


"But what am I?
An infant crying in the night:
An infant crying for the light:
And with no language but a cry."

**Alfred Tennyson**

# ኢትዮጵያዊት ሆሜር ...

ከገጽ 58 የቀጠለ

ከተመሠረቱት የቅኔ መልኮች እማሆይ የሚጠቀሙባቸው :- ጉባኤ ቃና ፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኑ፣ ዋዜማ፣ ሥላሴ ዘይእዜና መወድስ ቅኔ መሆናቸውን ሰለሞን ሐዲስ በዲግሪ ሟሟያ ጽሑፋቸው ውስጥ ያብራራሉ።

## ማጠቃለያ

እማሆይ ገላነሽ በቅኔ ጥበብ ዕውቀትና በፅኑ መንፈሳቸው ብርሃን እየተመሩ የኖሩ ማየት የተሳናቹው ሊቅ ነበሩ። እማሆይ የጐንጅና የፅላሎን የቅኔ ጐዳና የመረመሩ፣ የመሠጠሩ የተረጎሙና ያቀኑ ፋና ወጊ የሴት ባለቅኔ ነበሩ። የእማሆይ የቅኔ ጭማቂ አንጀት የሚያርስ፣የምሥጢሩ መዓዛ ሕይወትን የሚያውድ እንደነበር ሰለሞን ሐዲስ በጥናታዊ ጽሑፋቸው ያመላክታሉ። እማሆይ በአንድ በኩል ማየት የተሳናቸው በመሆናቸው በሌላ በኩል በቅኔያቸው ረቂቅነትና ምጥቀት የኢሊያድና ኦዲሴ ደራሲ ከሆነው ባለቅኔ ሆሜር ጋር በማመሳሰል "ኢትዮጵያዊቷ ሆሜር" ሊባሉ እንደሚችሉ ብዙዎች ይስማማሉ።


## የመረጃ ምንጮች መዘርዝር

ሰለሞን ሐዲስ። 1992 ዓ.ም "የእማሆይ ገላነሽ የሕይወት ታሪክ" በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ያልታተመ ጽሑፍ።

ቀሲስ ከፍያለው መራሒ። 1978፣ ሴቶች በኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ፣ የት.መ.ማ.ማ ድርጅት

ተሾመ ሐዲስ ። ቃለ መጠይቅ። በሰለሞን ሐዲስ የጥናት ጽሑፍ የቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባይ